| | |
|---|---|
| ለመባ መሰብሰቢያ የሚሆኑ | |
| ከወርቅ የተሠሩ ሳሕኖች | 30 |
| ለመባ መሰብሰቢያ የሚሆኑ | |
| ከብር የተሠሩ ሳሕኖች | 1,000 |
| ሌሎች ልዩ ልዩ ዕቃዎች | 29 |
| ከወርቅ የተሠሩ ታናናሽ ዕቃዎች | 30 |
| ከብር የተሠሩ ታናናሽ ዕቃዎች | 410 |
| ሌሎች ልዩ ልዩ ዕቃዎች | 1,000 |

11 ሼሽባጻር ከሌሎቹ ስደተኞች ጋር ሆኖ
ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም በተመለሰ ጊዜ ያመ
ጣቸው ከብርና ከወርቅ የተሠሩ ዕቃዎችና ሌሎ
ቹም ንዋያተ ቅድሳት ድምር 5,400 ነበር ።

## ምዕራፍ 2

### ወደ ሀገራቸው የተመለሱት እስራኤላውያን ስደተኞች ዝርዝር
(ነሀ. 7፥4-73)

1 ከስደተኞች ብዙዎቹ ከባቢሎን ክፍለ ሀገር
በመነሣት ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ ይሁዳ
ምድር ተመልሰው እያንዳንዱ ወደ መኖሪያ
ከተማው ገባ፤ እነርሱም የባቢሎን ንጉሥ ናቡ
ከደነፆር ማርኮ ከወሰዳቸው ጊዜ ጀምሮ ከነቤተ
ሰቦቻቸው በባቢሎን ምድር ስደተኞች ሆነው
የኖሩ ነበሩ ። 2 ለተመለሱትም ስደተኞች መሪ
ዎች ሆነው የመጡት ዘሩባቤል ፥ ኢያሱ ፥ ነህ
ምያ ፥ ሠራያ ፥ ረዔላያ ፥ መርዶክዮስ ፥ ቢል
ሻን ፥ ሚስፓር ፥ ቢግዋይ ፥ ሬሁምና በዓና ተብ
ለው የሚጠሩት ነበሩ ። ከእያንዳንዱ እስራኤላዊ
ጐሣ በመሰባሰብ ወደ ሀገር የተመለሱትም ስደ
ተኞች ዝርዝር ከዚህ የሚከተለው ነው ፦

| | |
|---|---|
| 3-20 ከፓርዖሽ ወገን | 2,172 |
| ከሸፋጥያ ወገን | 372 |
| ከአራሕ ወገን | 775 |
| ከፓሐትሞአብ ወገን የዬሹዓና | |
| የኢዮአብ ዝርያዎች | 2,812 |
| ከዔላም ወገን | 1,254 |
| ከዛቱ ወገን | 945 |
| ከዛካይ ወገን | 760 |
| ከባኒ ወገን | 642 |
| ከቤባይ ወገን | 623 |
| ከዓዝጋድ ወገን | 1,222 |
| ከአዶኒቃም ወገን | 666 |
| ከቢግዋይ ወገን | 2,056 |
| ከዓዲን ወገን | 454 |
| በሕዝቅያስ በኩል ከአጤር ወገን | 98 |
| ከቤጻይ ወገን | 323 |
| ከዮራ ወገን | 112 |
| ከሐሹም ወገን | 223 |
| ከጊባር ወገን | 95 |

21-35 ከስደት ከተመለሱትም ሕዝብ መካከል
በተለይ የቀድሞ አባቶቻቸው ከዚህ በሚከተ
ሉት ከተሞች ይኖሩ የነበሩት ዝርዝር ይህ
ነው ፦

| | |
|---|---|
| የቤተልሔም ተወላጆች | 123 |
| የነጦፋ ተወላጆች | 56 |
| የዐናቶት ተወላጆች | 128 |
| የዓዝማዌት ተወላጆች | 42 |
| የቂርያትይዓሪም ፥ የከፊራና | |
| የበኤሮት ተወላጆች | 743 |
| የራማና የጌባዕ ተወላጆች | 621 |
| የሚክማስ ተወላጆች | 122 |
| የቤትኤልና የዐይ ተወላጆች | 223 |
| የነቦ ተወላጆች | 52 |
| የማግቢሽ ተወላጆች | 156 |
| የሌላይቱ ዔላም ተወላጆች | 1,254 |
| የሓሪም ተወላጆች | 320 |
| የሎድ ፥ የሐዲድና የኦኖ ተወላጆች | 725 |
| የኢያሪኮ ተወላጆች | 345 |
| የሰናአ ተወላጆች | 3,630 |

36-39 ከዚህ የሚከተለው ደግሞ ከስደት የተ
መለሱ የካህናት ቤተሰብ ዝርዝር ነው ፦

| | |
|---|---|
| የዬሹዓ ዝርያ የሆነው | |
| የይዳዕያ ቤተሰብ | 973 |
| የኢሜር ቤተሰብ | 1,052 |
| የፓሽሑር ቤተሰብ | 1,247 |
| የሓሪም ቤተሰብ | 1,017 |

40-42 ከስደት የተመለሱት የሌዋውያን ቤተሰ
ቦች ዝርዝር እንደሚከተለው ነው ፦

| | |
|---|---|
| የሆዳውያ ዝርያዎች የሆኑት የዬሹዓና | |
| የቃድሚኤል ቤተሰቦች | 74 |
| የአሳፍ ዝርያዎች የሆኑት የቤተ | |
| መቅደስ መዘምራን ብዛት | 128 |
| የቤተ መቅደስ ዘብ ጠባቂዎች የሆኑት | |
| የሻሉም ፥ የአጤር ፥ የጣልሞን ፥ የዓ | |
| ቁብ ፥ የሐጢጣና የሾባይ ዝርያዎች | 139 |

43-54 ለቤተ መቅደስ ሥራ ከተመደቡትም
መካከል ከስደት የተመለሱት ጐሳዎች የሚከተ
ሉት ናቸው ፦

ጺሐ ፥ ሐሡፋ ፥ ጣባዖት ፥
ቄሮስ ፥ ሲዓሃ ፥ ፋዶን ፥
ለባና ፥ ሐጋባ ፥ ዓቁብ ፥
ሐጋብ ፥ ሻምላይ ፥ ሐናን ፥
ጊዴል ፥ ጋሐር ፥ ረአያ ፥
ረጺን ፥ ነቆዳ ፥ ጋዛም ፥
ዑዛ ፥ ፓሴሐ ፥ ቤሳይ ፥
አስና ፥ መዑኒም ፥ ነፊሲም ፥
ባቅቡቅ ፥ ሐቁፋ ፥ ሐርሑር ፥
ባጽሉት ፥ መሒዳ ፥ ሐርሻ ፥
ባርቆስ ፥ ሲስራ ፥ ቴማሕ ፥
ነጺሐና ሐጢፋ ።

55-57 ከሰሎሞን አገልጋዮችም ወገን ከስደት
የተመለሱት ጐሳዎች ፥

ሶጣይ ፥ ሀሶፌሬት ፥ ፐሩዳ ፥
ያዕላ ፥ ዳርቆን ፥ ጊዴል ፥
ሽፋጥያ ፥ ሐጢል ፥ ፖኬሬት ፥
ሐጸባይምና አሚ ተብለው የሚጠሩ ናቸው ።

### ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ

31 ከአሀዋ ወንዝ ተነሥተን ወደ ኢየሩሳሌም
ጕዞ የጀመርነውም የመጀመሪያው ወር በገባ
በዐሥራ ሁለተኛው ቀን ነበር፤ በምንጓዝበትም
ጊዜ አምላካችን ከእኛ ጋር ስለነበር ከጠላት
አደጋና ከደፈጣ ተዋጊዎች ሽመቃ ጠበቀን።
32 ኢየሩሳሌም በደረስንም ጊዜ በዚያ የሦስት
ቀናት ዕረፍት አደረግን፤ 33 ከዚህም በኋላ በአ
ራተኛው ቀን ወደ ቤተ መቅደስ ሄድን፤
ብሩን፥ ወርቁንና ንዋያተ ቅድሳቱንም ሁሉ
መዝነን ለኡሪያ ልጅ ለካህኑ ለመሬሞት አስረከ
ብነው፤ የፊንሐስ ልጅ ኤልዓዛርና እንዲሁም
ዮዛባድ ተብሎ የሚጠራው የኢያሱ ልጅና ኖዓ
ዲያ ተብሎ የሚጠራው የቢኑይ ልጅ ከእርሱ
ጋር አብረው ነበሩ። 34 ሁሉም ነገር በዚያኑ
ሰዓት ተቈጥሮና ተመዝኖ በትክክል ተመዘገበ።
35 ከዚያም ቀጥሎ እነዚያ ከስደት የተመለ
ሱት ሕዝብ ሁሉ ለእስራኤል አምላክ የሚቃ
ጠል መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርበውን መባ ሁሉ
አመጡ፤ በዚህ ዐይነት በመላው እስራኤል
ሕዝብ ስም ዐሥራ ሁለት ኮርማዎችን፥ ዘጠና
ስድስት የበግ አውራዎችንና ሰባ ሰባት የበግ
ጠቦቶችን አቀረቡ፤ እንዲሁም ስለ ኃጢአታ
ቸው ስርየት ዐሥራ ሁለት አውራ ፍየሎችን
አቀረቡ። 36 ንጉሡ ንጉሡ የሰጣቸውንም ሰነድ
በኤፍራጥስ ምዕራባዊ ክፍለ ሀገር ሳሉት ገዢዎ
ችና ባለሥልጣኖች አቀረቡ፤ እነርሱም ሕዝቡ
ንና የእግዚአብሔርን ቤት ሥራ በማገዝ ድጋፉ
ቸውን ሰጡ።

## ምዕራፍ 9

### ዕዝራ ከአይሁድ ዘር ውጭ የተደረገ ጋብቻ መኖሩን ተነዘበ

1 ይህም ሁሉ ከተፈጸመ በኋላ ከእስራኤል
ሕዝብ መሪዎች አንዳንዶቹ ወደ እኔ ቀርበው
ከዚህ የሚከተለውን ቃል ነገሩኝ፥ "ሕዝቡና
ካህናቱ ሌዋውያኑም ጭምር በጐረቤት ባሉት
በዐሞን፥ በሞአብና በግብጽ ከሚኖሩትና እንዲ
ሁም ከከነዓናውያን፥ ከሒታውያን፥ ከፌሪዛው
ያን፥ ከኢያቡሳውያንና ከአሞራውያን ርኵሰት
ራሳቸውን አልጠበቁም፤ እነዚያ አረማውያን
ሕዝብ ሲፈጽሙት የነበረውን አስጸያፊ ነገር
ሁሉ አድርገዋል። 2 ምክንያቱም የአይሁድ
ሕዝብ ራሳቸው ከባዕዳን ሴቶች ጋር ጋብቻ
በመፈጸማቸው የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝብ
ረክሰዋል፤ ለዚህም በቀድሚያ አሰናካዮች የሆ
ኑት መሪዎችና ባለሥልጣኖቹ ናቸው።"
3 እኔም ይህን በሰማሁ ጊዜ በሐዘን መጐናጸፊያ
ዬንና ካባዬን ቀደድሁ፤ የራስ ጠጕሬንና
ጢሜን በመንጨት በብርቱ ሐዘን ላይ ሆኜ ተቀ
መጥሁ፤ 4 የሠርክ መሥዋዕት እስከሚቀርብበ
ትም ጊዜ ድረስ በድንጋጤና በሐዘን ቆየሁ፤
የእስራኤል አምላክ የሆነ እግዚአብሔር ከስደት
የተመለሱት ሕዝብ ስለሠሩት ኃጢአት በተናገ
ረው ቃል ከመፍራት የተነሣ ድንጋጤ አድሮባ
ቸው የነበሩትም ሁሉ በዙሪያዬ ተሰበሰቡ።
5 የምሽትም መሥዋዕት የሚቀርብበት ሰዓት
በደረሰም ጊዜ በሐዘን ከተቀመጥሁበት ስፍራ
ተነሣሁ፤ የቀደድሁትን ልብስ ለበስሁ፤ በጕል
በቴም በመንበርከክ ወደ አምላኬ ወደ እግዚአ
ብሔር እጆቼን ዘርግቼ እንዲህ ስል ጸለይሁ፥
6 "አምላኬ ሆይ! ራሴን ወደ አንተ ቀና ለማድ
ረግ እንኳ በብርቱ አፈርሁ፤ ኃጢአታችን ሁሉ
ከራሳችን በላይ ከፍ ብሎ እንደክምር በመሆን
እስከ ሰማይ ደርሶአል። 7 ከቀድሞ አባቶቻችን
ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ እኛ ሕዝብህ
ታላቅ በደል ሠርተናል፤ ከኃጢአታችንም
ብዛት የተነሣ እኛ ሕዝብህ፥ ነገሥታቶቻችንና
ካህናቶቻችን በባዕዳን ነገሥታት እጅ ወድቀ
ናል፤ ስለዚህም ለሰይፍ ተዳረግን፤ ሀብታችን
ንም ተዘረፍን፤ በመታሰር ተማርከን ተወሰ
ድን፤ እነሆ አሁንም እንዳለንበት ሁኔታ እስከ
መጨረሻ ተዋርደናል። 8 አምላካችን እግዚአብ
ሔር ሆይ! ዐይናችንን አበራህ፤ እነሆ አሁን
ደግሞ ለጥቂት ጊዜ በፊትህ ሞገስን አግኝተን
ከእኛ ጥቂቶቹ ከባርነት ቀንበር ነፃ ወጥተው
በዚህች ቅድስት ምድር በሰላም ይኖሩ ዘንድ
ፈቅደሃል፤ ምንም እንኳ በባርነት አገዛዝ ሥር
ብንወድቅም እነሆ አዲስ ሕይወት ሰጥተኸ
ናል። 9 እኛ ባሮች ነበርን፤ አንተ ግን ባሮች
ሆነን እንድንቀር አልተውኸንም፤ አንተ የፋርስ
ነገሥታት እንዲራሩልንና በሕይወት ነፃ ወጥ
ተን ቀደም ሲል ፈርሶ የነበረውን ቤተ መቅደስ
ዘን እንደገና መልሰን እንድንሠራ፥ እዚህም
በይሁዳና በኢየሩሳሌም በሰላም እንድንኖር ፈቀ
ድህልን።
10 "ነገር ግን አምላክ ሆይ! እስከ አሁን ስለ
ሆነው ነገር ሁሉ ምን ማለት እንችላለን? እነሆ
አሁንም እንደገና ትእዛዛትህን ተላልፈናል፤
11 እነዚህም ትእዛዛት በአገልጋዮችህ በነቢያት
አማካይነት የተሰጡ ነበሩ፤ ነቢያት አስቀድ
መው 'የምትወርሱአት ምድር ከርኲሰት ሁሉ
የነጻች አይደለችም፤ ምክንያቱም የሚኖሩባት
ሕዝብ ዳር እስከዳር በአስጸያፊ ተግባር ሁሉ
እንድትሞላ አድርገዋታል' ሲሉ ነግረውን
ነበር፤ 12 አገሪቱን ወርሰን እስከ ዘላለሙ ልንደ
ሰትባት፥ ለልጅ ልጆቻችን ማስተላለፍ ከፈለ
ግን፥ ከእነዚያ አረማውያን ጋር ጋብቻ መፈ
ጸም እንደማይገባንና በምድሪቱ ላይ በልጽገው
በተሟላ ሁኔታ ይኖሩ ዘንድ ልንፈቅድላቸው

9፥12 ዘፀ. 34፥11-16፤ ዘዳ. 7፥1-5።

አብራምን መርጠህ ወደዚህ
መራኸው ፤
ስሙንም ለውጠህ ‘አብርሃም’ ብለህ
ጠራኸው ።
8 እርሱም ለአንተ ታማኝ እንደሆነ
ተመልክተህ ፥
ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳንን አደረግህ ፤
ከነዓናውያን ፥ ሒታውያን ፥
አሞራውያን ፥
ፌሪዛውያን ፥ ኢያቡሳውያንና
ጌርጌሳውያን የሚኖሩባትንም
የከነዓንን ምድር ለዘርያዎቹ
መኖሪያ ርስት አድርገህ ልትሰጠው ቃል
ገባህለት ፤
አንተ ታማኝ ስለሆንህ ቃል ኪዳንህን
አጽንተህ ጠብቀሃል ።

9 “አንተ የቀድሞ አባቶቻችን በግብጽ
የደረሰባቸውን መከራ አየህ ፤
ቀይ ባሕር አጠገብ ሆነው
እንድትረዳቸው ያቀረቡትን ልመና
ሰማህ ።
10 በግብጽ ንጉሥ ላይ በባለሥልጣኖቹና
በምድሩ
በሚኖሩትም ሕዝብ ሁሉ ላይ
ድንቅ ተአምራትን ገልጠህ አሳየህ ።
ይህንንም ማድረግህ እነርሱ ሕዝብህን
እንዴት እንደሚጨቁኑ በማየትህ
ነው ፤
ይህንንም በማድረግህ እስከ ዛሬ ድረስ
የማይረሳውን የታላቅነት ዝና ለራስህ
አስገኝተሃል ።
11 ባሕሩን ለሁለት ከፍለህ መንገድ
በማበጀት
ሕዝብህን በደረቅ ምድር
አሻገርሃቸው ፤
ድንጋይ ወደ ጥልቅ ባሕር
እንደሚጣል ፥
እነርሱን ያሳድዱ የነበሩትንም
ጠላቶቻቸውን በባሕር ውስጥ
ሰጥመው እንዲቀሩ አደረግህ ።
12 በቀን በደመና ዐምድ መራሃቸው ፤
በሌሊትም መንገዳቸውን በእሳት
ዐምድ አበራህላቸው ።
13 ከሰማይ ወርደህ ሕዝብህን በሲና ተራራ
ላይ አነጋገርሃቸው ፤
መልካም የሆኑትን ሕግጋትና
ጠቃሚ ትምህርቶችንም ሰጠሃቸው ።
14 የተቀደሰውን ሰንበትህንም እንዲያከብሩ
አስተማርሃቸው ፤
በአገልጋይህም በሙሴ አማካይነት
ሥርዓትህን ፥ ትእዛዛትህንና ሕግጋትህን
ሰጠሃቸው ።

15 “በተራቡም ጊዜ ምግብን ከሰማይ
ሰጠሃቸው ፤
በተጠሙም ጊዜ ውሃን ከአለት
አፈሰቅህላቸው ፤
ለእነርሱ ልትሰጣቸው ቃል
የገባህላቸውንም ምድር
በቊጥጥራቸው ሥር ያደርጉ ዘንድ
አዘዝሃቸው ።
16 ነገር ግን የቀድሞ አባቶቻችን
ትዕቢተኞችና እልኸኞች ሆኑ ፤
በሕግህ መመራትንም እምቢ አሉ ፤
17 ታዛዦችም አልሆኑም ፤
ያደረግህላቸውንም ተአምራት ሁሉ
ረሱ ፤
ከትዕቢታቸውም የተነሣ በማመፅ ፥
ከመካከላቸው መሪ መርጠው
እንደገና ወደ ግብጽ ባርነት
እንዲመራቸው አደረጉ ፤
አንተ ግን በፍቅር የተሞላህ ፥
ለቊጣ የዘገየህ ፥ ይቅር ባይ ፥
ቸርና መሐሪ አምላክ በመሆንህ
አልተውሃቸውም ።
18 እነርሱ በጥጃ አምሳል ጣዖትን ለራሳቸው
ሠርተው
‘ከግብጽ መርቶ ያወጣን አምላክ ይህ
ነው’ አሉ ።
አምላክ ሆይ! ምንኛ ስምህን አጐደፉ!
19 ነገር ግን ምሕረትህ ታላቅ ከመሆኑ
የተነሣ ፥
በዚያ ምድረ በዳ ይጠፉ ዘንድ
አልተውሃቸውም ፤
በቀንና በሌሊት የሚመራቸውን
ደመናውንም ሆነ የእሳቱን ብርሃን
አላራቅህባቸውም ።
20 ሊያደርጉት የሚገባቸውን ሁሉ
እንዲያውቁ ቸር መንፈስህን
ሰጠሃቸው ፤
የሚመገቡትን መና ፥ የሚጠጡትንም
ውሃ ሰጠሃቸው ።
21 አርባ ዘመን ሙሉ በበረሓ ሲጓዙ
ከሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ ምንም
አላሳጣሃቸውም ፤

9፥8 ፦ ዘፍ. 15፥18-21። 9፥9 ፦ ዘጸ. 3፥7፤ 14፥10-12። 9፥10 ፦ ዘጸ. 7፥8–12፥32።
9፥11 ፦ ዘጸ. 14፥21-29፤ 15፥4-5። 9፥12 ፦ ዘጸ. 13፥21-22። 9፥13-14 ፦ ዘጸ. 19፥18–23፥33።
9፥15 ፦ ዘጸ. 16፥4-15፤ 17፥1-7፤ ዘዳ. 1፥21። 9፥16-17 ፦ ዘኁ. 14፥1-4፤ ዘዳ. 1፥26-33። 9፥17 ፦ ዘጸ. 34፥6፤
ዘኁ. 14፥18። 9፥18 ፦ ዘጸ. 32፥1-4። 9፥19-21 ፦ ዘዳ. 8፥2-4።

2-7 ካህናት ፡-
ሡራያ ፥ ኤርምያስ ፥ ዕዝራ ፥
አማርያ ፥ ማሉክ ፥ ሐጡሽ ፥
ሽካንያ ፥ ረሁም ፥ መሬሞት ፥
ዒዶ ፥ ጊነቶን ፥ አቢያ ፥
ሚያሚን ፥ መዓድያ ፥ ቢልጋ ፥
ሸማዕያ ፥ ዮያሪብ ፥ ይዳዕያ ፥
ሳሉ ፥ ዓሞክ ፥ ሒልቂያና ይዳዕያ ።
እነዚህ ሰዎች ስሊቀካህናቱ በኢያሱ ዘመን
የወገኖቻቸው ካህናት መሪዎች የነበሩ ናቸው ።

8 ሌዋውያን ፡-
የምስጋና መዝሙር ኀላፊዎች የነበሩት ሌዋ
ውያን ዬሹዓ ፥ ቢኑይ ፥ ቃድሚኤል ፥ ሼሬ
ብያ ፥ ይሁዳና ማታንያ ነበሩ ።
9 በመቀባበል የሚቀርበውንም መዝሙር አዘ
ጋጆች ፡- ባቅቡቅያ ፥ ዑኖና ሌሎችም ሌዋው
ያን ወንድሞቻቸው ነበሩ ።

### የሊቀ ካህናቱ የኢያሱ ዝርያዎች

10 ኢያሱ ዮያቂምን ወለደ ፤ ዮያቂም ኤልያ
ሺብን ወለደ ፤ ኤልያሺብ ዮያዳዕን ወለደ ፤
11 ዮያዳዕ ዮናታንን ወለደ ፤ ዮናታን ያዱዓን
ወለደ ።

### የካህናት ጐሳ አለቆች

12-21 ዮያቂም ሊቀካህናት በነበረበት ዘመን
ከዚህ የሚከተሉት ካህናት ፥ የካህናት ጐሣዎች
አለቆች ነበሩ ፡-

| ካህኑ | ጐሳው |
|---|---|
| መራያ | ሡራያ |
| ሐናንያ | ኤርምያስ |
| መሹላም | ዕዝራ |
| የሆሐናን | አማርያ |
| ዮናታን | መሉኪ |
| ዮሴፍ | ሸባንያ |
| ዓድና | ሓሪም |
| ሔልቃይ | መራዮት |
| ዘካርያስ | ዒዶ |
| መሹላም | ጊነቶን |
| ዚክሪ | አቢያ |
| ...[1*] | ሚንያሚን |
| ፒልጣይ | ሞዓዲያ |
| ሻሙዐ | ቢልጋ |
| የሆናታን | ሸማዕያ |
| ማትናይ | ዮያሪብ |
| ዑዚ | ይዳዕያ |
| ቃላይ | ሳላይ |
| ዔቤር | ዓሞቅ |
| ሐሻብያ | ሒልቂያ |
| ናትናኤል | ይዳዕያ |

### የካህናትንና የሌዋውያንን ቤተሰቦች ስም ዝርዝር የሚገልጥ መዝገብ

22 ኤልያሺብ ፥ ዮያዳዕ ፥ ዮናታንና ያዱዐ
ተብለው የሚጠሩት ሊቃነ ካህናት በኖሩበት
ዘመን የሌዋውያንና የካህናት ቤተሰብ አለቆች
ተለይተው የሚታወቁበት መዝገብ ተዘጋጅቶ
ነበር ፤ ይህም መዝገብ የተዘጋጀው ዳርዮስ የፋ
ርስ ንጉሠ ነገሥት በሆነበት ዘመን ነበር ።
23 ይሁን እንጂ የሌዋውያን ቤተሰብ አለቆች
በግልጽ መዝገብ የታወቁት የኤልያሺብ የልጅ
ልጅ የሆነው ዮናታን በሕይወት እስከኖረበት
ዘመን ብቻ ነበር ።

### በቤተ መቅደስ የአገልግሎት አመዳደብ

24 ሌዋውያኑ በሐሻብያ ፥ በሼሬብያ ፥ በዬ
ሹዓ ፥ በቢኑይና በቃድሚኤል መሪነት በሁለት
ቡድኖች ተከፈሉ ። ሁለቱም ቡድኖች የእግዚአ
ብሔር ሰው የሆነ ንጉሥ ዳዊት በሰጠው መመ
ሪያ መሠረት እየተቀባበሉ የምስጋና መዝሙር
በማቅረብ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር ።
25 በቤተ መቅደሱ ቅጽር በር አጠገብ የተሠ
ሩትን የዕቃ ግምጃ ቤቶች የሚጠብቁ ዘበኞችም
ማታንያ ፥ ባቅቡቅያ ፥ ዖባድያ ፥ መሹላም ፥
ጣልሞንና ዓቁብ ተብለው የሚጠሩት ነበሩ ።
26 እነዚህም የኢዮጼዴቅ የልጅ ልጅ የሆ
ነው የኢያሱ ልጅ ዮያቂም ፥ አገረ ገዥው ነህ
ምያና የሕግ ምሁር የሆነው ካህኑ ዕዝራ በነበሩ
በት ዘመን የተመደቡ አገልጋዮች ነበሩ ።

### ነህምያ የኢየሩሳሌምን ከተማ ቅጽር ግንብ የምረቃ በዓል አደረገ

27 የኢየሩሳሌም ከተማ ቅጽር ግንብ የምረቃ
በዓል በተከበረበት ዕለት ሌዋውያኑ ከየሚኖሩ
በት ስፍራ ተፈልገው መጡ ፤ ስለዚህም እነርሱ
በጸናጽል ፥ በበገናና በመሰንቆ ዜማ የተቀናበረ
የምስጋና መዝሙር በማቅረብ የምረቃውን
በዓል ለማድመቅ ችለዋል ። 28 ይህንንም በዓል
ለማክበር የሌዋውያኑ ቤተሰቦች መዘምራን ሁሉ
ሰፍረው ከነበሩበት ከኢየሩሳሌም አካባቢና በነ
ጦፋ ከሚገኙት ታናናሽ ከተሞች ፥ 29 ከቤትጊ
ልጋል ፥ ከጌባዕና ከዓዝማዌት ተሰብስበው
መጡ ፤ 30 ካህናቱና ሌዋውያኑም ስለራሳቸው ፥
ስለ ሕዝቡ ፥ ስለ ቅጽር በሮቹ ፥ ስለ ከተማይቱ
የቅጽር ግንብ የማንጻትን ሥርዓት ፈጸሙ ።
31 እኔም ነህምያ የይሁዳን መሪዎች በቅጽሩ
ግንብ ላይ ሰብስቤ መዘምራኑን በሁለት ታላላቅ
ቡድን በመከፈል እግዚአብሔርን እያመሰገኑ
በመዘመር ተሰልፈው ከተማይቱን እንዲዞሩ አደ
ረግሁ ።

1* 12፥17 በዕብራይስጡ በዚህ ቦታ የሰውዬው ስም የለም ።

